# ዴሞክራሲያ

ዴሞክራሲያ ቅጽ 36 ቁጥር 1 መስከረም 2003 ዓ.ም.

## የምን ዕንቁጣጣሽ?--አዲስ ዓመት፤ ቀጣይ መከራ!

ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ መልካም አዲስ ዓመት ይሁንልህ ይሁንልሽ መባባል ልምድ ሆኖ ይህን የዕንቁጣጣሽ መልዕክት ያጅብ የነበረው ተስፋ ግን ከዓመት ዓመት እየደበዘዘና ድራሹም እየጠፋ እንዲያውም አዲሱ ዓመት ያለፈውን መከራና ቃይ አጠናክሮ እንደሚመጣ እርግጠኛ እየተሆነ መገኘት የተለመደ ሆኗል።

ግፍና መከራ፣ ስየልና ሰቆቃ፣ ፍጅትና በደል ጎልቶ በታየበት ያለፈው ዓመት የተደመደመው፤ የመለስ ቡድን የመድብለ ፓርቲ ጭምብሉን አውልቆ የአንድ ድርጅት አገዛዝ ይፋ ሲያደርግ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። ይህ ፀረ ሕዝብ ቡድን የሀገራችንን መሬት ሰፋ ባለ ደረጃ ለባዕዳን መሸጡን ገፍቶበት ታይቷል። ሱዳንም በቋራ እንደሰፈረ አለ። አምባገነኑና ሚስቱ ከጭፍሮቻቸው ጋር ሆነው በተሳለና ባገጠጠ ጥርሳቸው ኢትዮጵያን እየቦጫጨቋት ናቸው። የሕዝብን ሰብዓዊ መብት ረገጣው ብሶ እንጂ ቀንሶም አልታየም። ሰፊው አርሶ አደር ሕዝብ ከዓመት ዓመት መከራው ድርብ ድርብርብ ሆኖ ቀጥሏል። ወያኔ መንግሥት ነኝ ብሎ በመሬት ባለቤትነት ሲቀጥል ኩባንያዎቹ ደግሞ ከአርሶ አደሩ ምርት ቀማኛ ሆነዋል። ወያኔ ዛሬም ካዋሳኝ ጠቅላይ ግዛቶች ለም መሬቶችን እየወሰደ ከራሱ ክልል ማስገባቱን ቀጥሏል። ባዕዳን በሀገሪቷ ለም መሬት ዋና ተጠቃሚ ሆነው አንዳንዶቹም በዘረኝነት ዜጎችን እያጠቁና በአስጊ ደረጃም እግራቸውን እየተከሉ መሆናቸው ሲታይ ከሁሉም በላይ ግን በአባይ ወንዝ የተነሳ የኢትዮጵያን መዳከምና መበታተን ለምትፈልገው ግብፅ ሀገሪቷን ቧ አድርጎ ከፍቶ ለጥቃት ማጋለጡ አሳሳቢ መሆኑ መጠቀስ ያለበት ሆኖ ይገኛል።

ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ የተራብ ሆድ ሲሞላ ሳይሆን ይበልጥ በጠኔ ሲጠቃ መታዘብ ግዴታ ሆኖብናል። ኤኮኖሚው አደገ ተመነደገ ብሎ ቢለፍፍም፤ ይህን የአገዛዙን ውሸት የዓለም ባንክ ቢያስተጋባውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ገፈቱን ቀማሽ ነወና ያደገወና የጨመረው መከራው ብቻ

መሆኑን አሳምሮ ያውቀዋል፡፡ የኑሮ ወድነት መቀነስ ሳይሆን እያሻቀበ ሲሄድ የብር ዋጋም ይበልጥ ደቆ የሕዝቡን አቅም አኮስሶታል፡፡ ታስቦ የሚታደረው እራት ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ መብቶችም ናቸውና ዛሬም ከ35 ሺ ያላነሰ ዜጋ በየማጎሪያው ቤት ይሰቃያል፡፡ የወያኔ የምስጢር ማጎሪያዎች በአዲስ አበባ ቦሌ ቪላዎች ጀምሮ በትግራይና ወሎ የጉደጓድ እስር ቤቶችም የሚታዩ ናቸው:: የፖለቲካ እስረኞች ላይ ስየል በገፍ ይፈፀማል፡፡ ከ1983 በፊትና ከዚያም በኋላ በወያኔ ተይዘው ደብዛቸው የጠፋ እስረኞች የደረሱበትና የደረሰባቸው እስከዛሬ ተደብቆ ይገኛል፡፡ ለይስሙላና ለተወሰነ ጊዜ ለማደናገሪያ አለ ይባል የነበረው የነፃ-ፕሬስ መብት ዛሬ ወድሟል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ይህ ዘረኛ አገዛዝ ማንነቱን ማለትም በፀረ ኢትዮጵያዊነቱ የሚገለፀውን ይዘቱን በገሀድ ለሕዝብ ሲያሳይ 19 ዓመታት ያለፉ ቢሆንም አንዳንዶች-- የተወሰኑት የአገዛዙ የድብቅ ቅጥረኞች ሌሎች ደግሞ ለመንቃተ ከ19 ዓመት በላይ የሆነ መረጃ የሚፈልጉ--ከዚህ አገዛዝ ጋር መደራደርና በሰላምም ዴሞክራሲን አስከብሮ መጓዝ ይቻላል ብለው ሲሰብኩ ተደምጠዋል፡፡ አገዛዙ ግን ማለትም የመለስ ዜናዊ ቡድን በተለመደ ዕብሪቱ ቀደም ብሎ የነበረችውን፤ ጭላንጭል ትባል የነበረችውንም ምርጫ ነክ ሁኔታም ከርችሞና ዘግቶ ሁሉንም ተቃዋሚ ተብዬዎች አሳፍሮ በይፋና በድፍረት የአንድ ፓርቲ አገዛዙን አስፍኗል፡፡ ጭምብሉ መውለቁና መድብለ ፓርቲ ይባል የነበረውም መጋለጡ ለታጋይ ክፍሎች ጠቃሚ መሆኑም ግልፅ ነው:: የአንድ ድርጅትና የአንድ ሰው (ከነሚስቱና ቤተሰቡ) አምባገነንነት ሰፍኖ ምን ልትሆኑ እያለ እየደነፋ ነው፡፡ ይህን ዘረኛ ቡድን ለሥልጣን ያበቁና ዛሬም የሚጋልቡት ባዕዳን ኃይሎችም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሰፍኗል ብለው የሚያጭበረብሩትም አፈር በልቶባቸዋል፡፡ ለኢትዮጵያ ብዙ ፓርቲ አያስፈልጋትም፤ ለኤኮኖሚ ዕድገቷ እንደ ቻይና አንድ ፓርቲ ቢገዛት ይሻላል መባል የተጀመረውም አለምክንያት አይደለም፡፡ የመለስ ፀረ መድብለ ፓርቲ፣ ፀረ ዴሞክራሲ አገዛዝ እርቃኑን ወጥቷልና ቡቱቶም ቢሆን ሊያለብሱት እየጣሩ ናቸው፡፡ ሕዝብ ግን ሐቁን ያውቃል፡፡

በመሆኑም ሕዝብ በወያኔ ያለፈው ምርጫ ቧልት አልተካፈለም፡፡ ማዕቀብ ይገባል ሲባሉ አልሰማ ብለው በወያኔ ሜዳ ሊሯሯጡ የሞከሩት ደግሞ በዓለም ፊት ተዋርደዋል፡፡ የምርጫው ሕግ ሳይቀየር፤ የምርጫው ኮሚሽን ነፃ ሳይሆን፤ የታሰሩት ሳይፈቱ፤ ...ወዘተ ዓይንን ጨፍኖ መሠረታዊ መርህን ዘንግቶ ወደ ምርጫ መግባቱ ቅሌት መሆኑን እንዲቀበሉ የወያኔ የምርጫ ውጤት አስገድዷቸዋል፡፡ ይህ አረመኔ አገዛዝ በሰላም ሳይሆን ከሥልጣን የሚወገደውም በኃይል ብቻ፤ በሕዝባዊ አመፅ ብቻ መሆኑን በመካድ አደናጋሪ ሌላ መንገድን መፍትሄ ብለው ያቀረቡትም ማፈር የግድ ሆኖባቸዋል፡፡ ነብርና ፍየል በአንድ በረት ይደሩ ባዮች፤ ነብሩ ማንነቱ አለመቀየሩን ለማሳመን ጥርሱን ሲያሳያቸው የሚይዙትና የሚጨብጡት አጥተዋል፡፡ የወያኔ

ሞገደኛ ታሪኩ ይረሳ ብንል እንኳን በ1997 ምርጫ በህገወጥ መንገድ ሽንፈቱን ሊሰርዝ ሲነሳ ስንቱን ንፁህ ዜጋ እንደገደለና ስንት ሺዎችንም ለእስር እንደዳረገ እናውቃለን። ትግሉን ለማስቀጠል ምንም ሌላ መገልበጫ ስትራተጂ ሳያዘጋጁ አርጩሜ ይዞ ጅብን መጋፈጥ መቃጣት በራስ ላይ ጥፋትን መጋበዝ መሆኑን በመካድና ጥራዝ ነጠቅ ጋንዲያዊ ጥቅሶችን በማዥጎድጎድ የሰላም ትግል ተብሎ ሲለፈፍ የቆየው በመሠረቱ አገዛዙን ጠቅሞታል። ላም አለኝ በሰማይ እንዲሉ ከአገዛዙ ፀፀትና መሻሻልን በከንቱ መጠበቁ የታጋዩን ጎራ ሲያደናግርና ሲያዳክም አገዛዙን ግን ከጥቃት አድኖታል። ያለፈው ምርጫና ውጤቱ ደግሞ በምንም ዓይነትና መንገድ ወያኔን በምርጫ መታገል የሚለው ለሕዝብ የሚበጅና የሚጠቅም አማራጭ ሊሆን አለመቻሉን አረጋግጧል። ስለዚህም ሕዝብን ለመጪው ምርጫ እንዘጋጅ ብለው ሊሰብኩ የተነሱት ክፍሎች በዕውን ለሕዝብ መቆማቸው መጠየቅ ያለበት ሆኗል። ሕዝብና ታጋይ ኃይሎች መዘጋጀት ያለባቸው ለምርጫ ሳይሆን ለሁለገብ ትግልና በዚሁም አማካይነት ለወያኔ አገዛዝ ውድቀትና መወገድ መሆን አለበት።

ሁኔታው ዓመት በዓመት ሲተካ የተቃዋሚ ኃይሎች ይዞታን መገምገም የግድ ያደርግብናል። የመለስ ቡድን በሥልጣን የቆየው በአፈናና ባዕዳን አርዳታ ቢሆንም የተቃዋሚ ድርጅቶች ስህተትና ድክመትም ለወያኔ እንደጠቀመው የታወቀ ነው። ራሳቸውን ተቃዋሚ ድርጅት ብለው የሰየሙት ሁሉም በተጨባጭና በእርግጥ ተቃዋሚ እንዳልነበሩ ጊዜ አሳይቷል። ህብረት መኖሩ ለወያኔ ውድቀት ጠቃሚ ሆኖ ሳለም በየጊዜው የተሞከሩት ህብረቶች ቃል ኪዳናቸውን በቀየሩ፣ ለወያኔ ማደር በጀመሩ፣ የግል ሥልጣን ጥም ባሸነፋቸው፣ በወያኔ አፈና ሻጥርና በድርጅቶቹም ደክመት የተነሳ የተጠበቀውን ግብ ሊያሟሉ አልቻሉም። ከሁሉም በላይ ትግልን የጎዳው ወዳጅና ጠላትን መለየት ማቃቱ መሆኑ ደግሞ የሚካድ አይደለም። ማንኛውም ድርጅት ሀ ብሎ ሲጀምር ጠላት ወዳጁን መለየትና ግቡንም ማወቅ አለበት። በተለይም እመራለሁ የሚሉት ድርጅቶች ሕዝብን በምንና በማን ላይ እንደሚያስተባብሩና ማንንስ ማስጠጋት ማቀፍ እንዳለባቸው በቅድሚያ ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው። ይህን በተመለከተ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች በተደጋጋሚ ስህተቶችን ፈፅመዋል። ዓመት ቢቀየርም፣ የመለስ አገዛዝ ፀረ-ዴሞክራሲነት ተደጋግሞ ቢገለፅም፣ የምርጫን መንገድ በመከተል የተገኘው ትርፍ ፍጅት ሆኖ ቢታይም፣ ለመጪው ምርጫ እንዘጋጅ የሚል ቀረርቶን የሚያሰሙ ክፍሎች ዛሬም አሉ። መለስ ቢሄድ ለገሠ ተተካ የሚሆን ሁኔታ አንጂ ከቶም ሌላ ለውጥ የዛሬ አምስት ዓመት የሚታይ አለመሆኑ የሚታወቅ ነው--እጅ አጣጥፎ ምርጫ ተብዬው ከተጠበቀ በተለይ። የመለስ አገዛዝ ጠላትነት ታምኖበትና ተረጋግጧል፣ ይህ አገዛዝ በምርጫም ሆነ በሰላም በምለላ ወይም አደብ በመግዛት የሚቀየር ወይም የሚሻሻል አለመሆኑንም መሠረት በማድረግ በሁለገብ ትግል ይህን

ዘረኛ አገዛዝ ለማስወገድ ተነሱ ብሎ መቀስቀስ ይገባል ማለት ነው:: ይህ ከተደረገ እውነትም አዲሱ ዓመት ለውጥን አመጣ ብሎ መደምደምና መደሰትም ይቻላል::

ለአገዛዙ የተባለው ለባዕዳኑም የሚሠራ ነው:: ዓመት ከዓመት ባዕዳንን "አውጡን!" ልመና ሲኾጎደጎድባቸው ቆይቷል:: በባዕድ ሀገሮች በርካታ ሰልፎች ተካሂደዋል:: አሜሪካን መለስን በቃህ ብላዋለች፤ ማንን ላስቀምጥላችሁ ብላ ጠይቃለች፤ እኛን ቢያስር አሜሪካን ትቆጣዋላች፤ አሜሪካን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዴሞክራሲን ልታሰፍን ተነስታለች፤ አለ አሜሪካ ፍቃድ ምንም ትግል ማካሄድ አይቻልም፤ ...ወዘተ እየተባለ ወደ ምዕራቡ ማንጋጠጥ ሲቀጥል አገዛዙ ወደ ምዕራብም ወደ ምሥራቅም ደፋ እያለ ጥቅሙን ሊያስጠብቅ ችሏል:: አዲስ ዓመት እውን ለውጥን ካበሰረ ሕዝብ በራሱ ትግል ላይ መተማመን መቻልና ለባዕዳንም በቆራጥ ትግሉ ትምህርትን መስጠት መቻል አለበት:: በተለይ አዲሱ ዓመት ሲገባ አፍጦና ዋና ሆኖ ያለው ሁኔታ የሀገሪቷን ለም መሬት በገፍ ለባዕዳን ለመስጠት እየተወሰደ ያለውን እርምጃ ይመለከታል:: ፀረ ኢትዮጵያ የሆነው የመለስ ቡድን ብዙ ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬትን (ከጋምቤላ፣ ጎጃም፣ ሸዋ፣ ...ወዘተ) ለባዕዳን (ቻይና፣ ሕንድ፣ ሳውዲ ዓረብያ፣ ግብፅ፣ ጅቡቲ ...ወዘተ) አስረክቧል:: እነዚህ ባዕዳን ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በዝብዘው የሚያመርቱትን በቀጥታ ወደ ሀገራቸው የሚወስዱ መሆናቸው ደግሞ የተረጋገጠ ነውና ከዚህ ሁኔታ ሕዝብ የሚያገኘው ትርፍ አለ ማለት የሚቻል አይደለም:: የመለስ ዓላማ አንድም ገንዘብ ሲሆን አንድ ሄክታር በአንድ ብር ለ99 ዓመታት እየሸጠ ብዙ ባያስገባም፤ ዋናው ግቡ ግን ፖለቲካዊ ድጋፍን ለማግኘት መሆኑ ይታያል:: የኢትዮጵያን መሬት በነፃ በዝብዙ ያላቸውን አገዛዝ ዕድሜ ለመራዘም ይሟሟታሉ ብሎ መደምደሙ ትክክል ነው:: ቻይና በዛምቢያ ውስጣዊ ፖለቲካና ምርጫ ጣልቃ ገብታ ልትጫወት የሞከረችውን ሚና ያስታውሷልና ነው:: ሕዝብ በዝምታ ሁኔታውን እያየ ከተገኘ ለም መሬቱን እያጣና ለባሰ መከራና ውርደት እየተዳረገ ስቃዩ ከዓመት ዓመት እየተባባሰ ይሄዳል::

"ዝምታ ለበግም አልበጃት" እንዲሉ እምቢታና ተቃዋሞ ከተዳፈነ ጨቋኞቹና በዝባዦቹ ምንም ሀዘኔታ ሳይኖራቸው ሕዝብና ሀገርን የሚያጠፉ ይሆናሉ:: ባዕዳን ብቻ ሳይሆኑ አገዛዙናከሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ሁሉ ሕዝብን እየናቁ መታበያቸው ገሀድ ከሆነ ቆይቷል:: አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድኻ በመሆኑና ይህም ሁኔታው አንገቱን እያስደፋውና ክብሩን እየተፈታተነው በመገኘቱ የሕዝብን እርምጃ በተገዢነትና በወኔ ቢስነት የወሰዱት የወርቁ ክልል ተወላጆችና በዝባዦች ብቻ ሳይሆኑ ከአገዛዙ የተሞዳሞዱት መሆናቸው እየታየ ነው:: የመለስ ቡድን በይፋ ልመናን ሕገ ወጥ ብሎ የኔ ብጤውን ከመኪና መንገድ ስላራቀው ደስ የሚላቸው ይህ ድኽነትን ማጥፋት ሳይሆን ድህን ማፈን ማጥቃት መሆኑ ያልገባቸው ወይም ቢገባቸውም ያስደሰታቸው ጥቂቶች

አይደሉም:: ከበርን ተመቸን ብለውም ሕዝብን የሚያንጓጥጡና ሰቆቃው የራሱ ጉዳይ ነው የሚሉም በርክተዋል:: ከበርን ብለው አምባገነኑን የሚያወድሱ ጭቆና የሚያስለቅሰውን ሕዝብ አላዋቂም የሚሉ አሉ:: ሁሉም በአንድ አቁማዳ ገብተው በሕዝብ ድል የሚወቀጡ መሆናቸው የሚያጠራጥር አይደለም:: ያን ቀን ለማምጣት ግን፤ ዓመት ከዓመት ስቃይና ውርደት ቀጣይ እንዳይሆን ለማስቆም ደግሞ ሕዝብ መነሳት ማመፅ እንዳለበት መታወቅ ያለበት ሐቅ ነው:: የተናቀው ሕዝብ መናቁ ስህተት መሆኑን ለናቂዎቹ ማሳየት አለበት:: ከዓመት ዓመት እየፎከተና እየለመነ ካለበት ሁኔታ ሊወጣ አይችልም የሚሉትን፤ የተዘባነኑበትን ወያኔዎች ሁሉ አምፆና አሸብሮ ኃይሉን ሊያሳያቸው ይገባል:: የነሱ ብልጥነት የለየለት ራስን ጎጂ ዕብሪት መሆኑንም ሊያስተምራቸው ያሻል:: ሕዝብን የናቁ መጨረሻቸው የከፋ መሆኑንም በተግባር ሊያሳያቸው ያስፈልጋል ማለትም ነው::

ከዚህ አንፃር ሕዝብ በራሱ ራሱን ለማስከበርና ሀገሩን ለመጠበቅ የሚያካሂደው የግዳጅ ትግል እንዳለ ሆኖ በድርጅት ደረጃ--መደራጀት ወሳኝ ነውና--መሪዎቼ የሚላቸው ቆራጥነትና ፅናት፤ ሕዝባዊነትና መርህ አክባሪነት የሚታይባቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት:: የሕዝብ መሪ ነን እያሉ ገና ባሩድ ሳይጤስ እግሬ አውጪኝ ወይም ከአምባገነኑ ስር መደፋት የሚቀናቸው፤ የሰፊውን ሕዝብ መናቅ ልክ እንደ ዘረኞቹ የተላበሱ፤ ሕዝባዊው ለውጥ መምጣቱ እነሱንም የሚያስፈራቸው--ምንኛ ቢንጫጩና ቢጮሁ ወይም ገደል ማሚቴዎችን ቢያሰማሩ-- የሕዝብ መሪ ሊባሉ አይገባም:: ሕዝብ ግዳጁን ለመወጣት ሲነሳ በጎበዝ አለቃ ደረጃ፤ በሚተማመኑ ህዋሳት አማካይነት፣ ...ወዘተ ቢሆንም መደራጀቱ ደግሞ አስፈላጊና በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም:: በትግል የተፈተኑ ድርጅቶች ዙሪያ መሰባሰብ ተገቢ ነው:: ድርጅት ስንልም ከፖለቲካ ድርጅት ሌላ፤ ሕዝብ በሲቪክ ማህበራት፣ በሙያ ማህበራት፣ በሕዝብ ማኅበራት አማካይነት መተሳሰር አለበት:: አረመኔው አገዛዝ የሕዝብን ሀቀኛ ድርጅቶች ህገ ወጥብሎ ከማሳደዱ ሌላ የሲቪክ ማህበራትን (የሠራተኛ፣ የአስተማሪ፣ ...ወዘተን) አፈራርሶ የራሱን ተለጣፊዎች ሰይሟል:: ሕዝብን፣ ድርጅትም ድምፅም ነፍጎ ለማዋከብ የተነሳውን አገዛዝ የሕዝብን ድምፅና ቦታ የነጠቁ ወይም ሊነጥቁ የጣሩም ድርጅቶችም ወደዱም ጠሉም ረድተውታል:: በአሁኑ ወቅት የሽማግሌዎች ኮሚቴ በሚል ወያኔ ሎሌዎቹን አሰልፎ በሕዝብ ላይ እየፈፀመ ያለው ሻጥርና በደል አንድ ምሳሌ ነው:: ስለዚህም ሕዝብ ማህበራቱንና ድርጅቶቹንም ማስመለስ መቻል አለበት:: በይፋ መታገል ባልተቻለበት ደግሞ ፍቱኑ መድኃኒት በህቡዕ መደራጀትና መታገል ነውናም፤ በህቡዕ መታገያ ጊዜ አልፏል፤ ትክክልም አይደለም የሚሉትን ጆሮ መንፈግ ያስፈልጋል:: የአገዛዙን አረመኔነትና በሌላም በኩል ደካማ ጎኖቹን በግንዛቤ በማስገባት ተገቢውን የትግል ስልት ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅ ነው:: ሰላማዊ

*ሰልፍና አድማ ባልተቻለበት የሙት ከተማ አድማና ሌሎች መንገዶችን በመከተል፤ በአገዛዙ ዕቅዶች ላይ ሻጥርን በመፈፀም፤ ...ወዘተ ጠላትን መጉዳት ይቻላል:: ደጀን ሀገር ከጠፋና ዙሪያው ገደል ከሆነም ለዚህም መውጫ የሚገኝለት ነው:: በመጨነቅ ብቻ መርዝን መድኃኒት ብሎ መጠጣቱ ያከትማል ማለት ነው::*

*የምን ዕንቁጣጣሽ ስንልም በደፈናው ለማማረርና ቀቢፀ ተስፋን ለማስተናገድ ሳይሆን መልካም አዲስ ዓመት ብሎ በበዓል ደረጃ ለመፈንደቅ የሚያስችል ሁኔታ ውስጥ ገና አልደረስንምለማለት ነው:: ታፍነው ደብዛቸው የጠፋው ወገኖቻችን፤ በየጉድጓዱና በዝዋይ፣ በዴዴሳ፣...ወዘተ የሚማቅቁት ብዙ ሺ ዜጎች፤ በየመንገዱ የሚያድሩ፣ የሚበሉትና የሚልሱት ያጡት ወገኖች ሁሉ፤ እንኳን በግ ወይም ዶሮ ሊያርዱ ቀርቶ ጉርሻ ያጡ ወንድም እህቶቻችን ሁሉ ስቃይ እየተቀበሉ ባሉበት አዲሱ ዓመት የፍስሐና የፈንጠዚያ ሊሆን አይችልም ለማለት ነው:: ከሁሉ በላይ ግን ያለውን አሰቃቂ ሁኔታ ለ19 ዓመታት መድገሙ በአንድ በኩል አላስፈላጊ ነው ለማለት ባይቻልም ዋናው ጉዳይ ግን ታዋቂው የፖለቲካ ፈላስፋ እንዳለው 'ዋናው ግዳጅ የዓለምን ይዞታ መረዳቱ ሳይሆን ዓለምን መለውጥ' ነውና ወያኔን ማሸነፍና ማስወገድ ላይ ሙሉ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል:: ለዚህም ታሪክ ቅርስ መሳሪያ ነውና ያለፈውን ታሪክ መገምገሙና በደም የተገበየውንም ተመክሮ ማጤኑ በጣም ወሳኝ ነው:: ያለፈውን ስህተት ሁሉ መድገም ጎጂ እንደሆነ ፤ የ1997ኡ ጥፋት በ2002 መድገሙ ትግላችንን እንደጎዳ ማወቅ ተገቢና ወቅታዊ ነው:: ይህ ከሆነ፤ ለወሳኙ ትግል ቆርጠን ከተነሳን፤ የወያኔን ሥርዓት ለማውደም ከቆረጥን፤ ከአስመሳዮች ሁሉ ለመላቀቅ ከወሰንን፤ ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ መከራችን በዝቶ ተበራክቶ መቀጠሉ ያበቃና የብሩህ ቀን ጎሕ ሊቀድ ይችላል:: ያኔና ያኔም ብቻ ዕውነትም ዕንቁጣጣሽ ማለትና መልካም አዲስ ዓመት ስንልም ሀቁን መናገር ይሆንልናል::*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!*